# መልኩን የሚቀያይረው ወያኔያዊ ተልዕኮ

ከኃይለ ልዑል ግርማ (ዋሽንግተን ዲሲ)

የቅንጅትን ሰላማዊ ትግል መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ አምኖና ደግፎት ኃያልነቱን በሚያዝያ 30 ቀን 1997 ዓ.ም ካሳየንና ውሳኔውን ደግሞ ግንቦት 7 ቀን ከሰጠ በኋላ ያንን ዓይነት አገር አንቀጥቅጥ ትግል ወያኔን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አሰናብቶት የድሉን ውጤት ሳይቀምሰው በውጭ ኃይሎችና በወያኔ አረመኔያዊ በትር ተመትቶ በውስጥ ሰርገው የገቡ የወያኔ ተላላኪዎች አማካኝነት ሊጨናገፍ ችሏል።

ያለጥርጥር የኢትዮጵያ ሕዝብ ድሉን መልሶ እንደሚቀዳጅ በእርግጠኛነት መናገር ሲቻል፤ በውስጥ ሰርጎ ገቦችና ሆዳሞች አማካኝነት የሕዝብ ትግል ተዳክሞ የድሉ ጊዜ እንዲጓተትና የወያኔ ዕድሜ እንዲራዘም ማድረጋቸው ጊዜያዊ ነው።

በቅንጅት አመራር ውስጥ የነዶክተር ብርሃኑ ቡድን ውስጣዊ ቡርቡራም ይህን የሕዝብ ትግል አቅጣጫ በማሳት፣ በመቆጣጠር፣ የውጭ ኃይሎች በሚሰጧቸው መመሪያ የወያኔን ዕድሜ ማራዘሚያ ሆኖ ማገልገል ነው። ግፋ ቢል እነ መለስ ከኋላ ሆነው እነ ብርሃኑ ነጋን ከፊት ሊያደርጉ ይችሉ ይሆናል።

በጣም ሊስተዋል የሚገባ ነገር አለ። በወያኔ 14 ዓመት የአምባገነንና ዘረኝነት አገዛዝ ተመችቷቸውና ተባባሪ ሆነው የኖሩትን፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ምን ደረሰበት ብለው ያልተቆረቆሩ፣ በወያኔ የወደቀ የትምህርት ሥርዓት ተምረውና ሲሰሩ የቆዩት አንድ ላይ በቀስተደመና ስም ተሰባስበው፣ ስንት ሲዋደቅ፣ ሲታሰር፣ ሲሰቃይ መስዋዕትነት ሲከፍል የኖረውን ክፍል ተደባልቀው ትግሉን ተቆጣጥረውና አቅጣጫ አስተው ለወያኔ እድሜ መራዘሚያ የሆኑትን ሰዎች ለይቶ ማወቅና ዳግም በእነርሱ ቃል ላላመሸንገል፣ በሚያደርጉት ድራማም ላለመሞኘት መጠንቀቅ ነው።

እነ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ እና ግብረአበሮቹ ከሕዝብ ገዳይ ጋር ውስኪ ሲጣጡና ቴኒስ ሲጫወቱ፣ በሀብትም ደረጃ ሚሊየነር ለመሆን የበቁ ሰዎች ኋላ የመጣ ዓይን አወጣ ዓይነት ሥራቸው ምን ያህል የሕዝቡን ትግል እንደጎተተው በዓይናችን ያየነው ነው። የቃሊቲ እስር ቤት ድራማ በጣም ብዙ ኢትዮጵያውያንን አታሏል። በቃሊቲ እስርኛ ስም እነ ብርሃኑ ነጋ ከአሜሪካኖች ጋር ሲዶልቱ፣ እስረኛውን በገንዘብ ሲደልሉ፣ ተስፋ ሲያስቆርጡ፣ ሲያስፈራሩና በውጭ ያለውን ደጋፊ ኃይል በእነ አንዳርጋቸው ጽጌ አማካኝነት ሲከፋፍሉ ነው የከረሙት። ቆራጥና ጀግና የሆኑትን የቅንጅት መሪዎች ስም ሲያጠፉና ሲከፋፍሉ ነው የቆዩት። በአንጻሩ የወያኔን የዘረኝነት በሽታ ቫይረስ እነ ብርሃኑ ነጋ ሲዘሩ እንደነበር ብዙ ማረጋገጫዎች ተገኝተዋል። ከእስር ቤት እንደወጡም "ኮሌክቲቭ ሊደርሽፕ" በሚል አፍራሽ አካሄድ የቅንጅትን አመራር ለመከፋፈል ሞክረዋል። በውጭ ያለውን ደጋፊ በከፍተኛ ደረጃ አበጣብጠዋል፣ ከፋፍለዋል፣ ግራ አጋብተዋል።

የአሜሪካ አገር ጉሮ ወሸባዬ ጉዞአቸውም እንኳን ችግር ሊፈቱ የበለጠ ከፋፍለው የእራሳቸውን ደጋፊ ይዘው ከሕዝብ ላይ በብዙ መቶ ሺህ ዶላር ሰብስበው ግማሹ አገር ቤት ሲሄድ ሌላው አሜሪካ ቀርቷል።

የዛሬ የእነ ብርሃኑ ነጋ /አንዳርጋቸው ጽጌ/ እና የእነ ብርቱካን ሚዴቅሳ ቡድን እውን ተለያይተዋልን? ብሎ መጠየቅ በጣም ተገቢ ነው። እነ ብርሃኑ ነጋ ከቅንጅት ፓርቲ እራሳችንን አግልለናን ብለው የአምስት ሰዎችን ስም ደርድረው መግለጫ አውጥተዋል። ብርቱካን ሚዴቅሳ ሌላ ፓርቲ ለማቋቋም ፊርማ አሰባስባ ማመልከቻ አስገብታ የራሷን መንገድ እየነጎደች ሲሆን የሚገርመው አሁንም "መሪያችን ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል ናቸው" እያሉ በስማቸው መነገዳቸው ነው። በሕግ አምላክ! ፈጽሞ የማይገናኝን ነገር መናገራቸው ለምንድ ነው? ብንል የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደማይከተላቸው ስለሚያውቁ በቅንጅት ፓርቲና በፕሬዚዳንቱ ስም ነግደው ሀሳባቸውን ለማሳካት ነው። ሞከሩ እንጂ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይቺን ቀርቶ የረቀቀ የወያኔን ተንኮል በሩቅ ያውቀዋል።

ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ቃሊቲ እያለ ውጭ አገር ሄዶ ለመቅረት መወሰኑን አስቀድሞ ታውቋል። ዋናው ምክንያት በውጭ ያለውን የተቃዋሚ ኃይል በተቃዋሚ ስም ለመያዝና የተቃውሞ ትግሉን ለማክሸፍ ነው። ሌላ ምክንያት የለውም። ከጥቂት ወራቶች በፊት ዩንቨርስቲው ዕድል ሰጥቶኝ ሥራ ሳልሰራ ቁጭ ብለህ አስብ ብሎኝ እያለ ሲቀባጥር ነበር። ነገሮችን ሲያመቻች ነው። የትኛው ዩንቨርስቲ ነው "ና የትጥቅ ትግል ጀምር" ብሎ ጥናት እንዲያካሂድ ወይም ሥራ የሚሰጠው? በአፍ ማታለል ብርሃኑ ነጋ ከነ በረከት ስምዖን ከነመለስ ዜናዊ የተማረውና የተካነው በመሆኑ አንዴ ማታለል ያለ ቢሆንም

ነጋ ጠባ ማታለል ግን አይችልም። ሚያዝያ 30 ቀን 1997 ዓም ሶስት ሚሊዮን ሕዝብ ሰልፍ ሲወጣ በሰልፉ ያልነበሩት ወይም እቤታቸው ቁጭ ያሉት እነ ብርሃኑ ነጋና እና ጓደኞቹ እነ መለስ፣ በረከት ነበሩ። ደሃው ሕዝብ ግን ከአዲስ አበባ ውጭ በአውቶብስ ተጉዞ ተካፍሏል።

ከምርጫው በኋላ ከነበየነ ጴጥሮስ ጋር በቅንጅትና ሕብረት ስም ሕዝብ የማያውቀውን ድርድር ከወያኔ ጋር አድርጎ የተፈራረመው ብርሃኑ ነጋ ነው። የመስከረም 22ን ሰላማዊ ሕዝባዊ አመጽን ጥሪ ከአሜሪካኖች ጋር ተመሳጥሮ "አድማው ቀርቷል" ብሎ በቴሌቭዥን ተናግሮ ያከሸፈው ብርሃኑ ነጋ ነው። ቃሊቲ እስር ቤት "እኛ የተማሩ ሰዎች አሉን ከእኛ ጋር ስሩ" እያለ የራሱን ግሩፕ በመፍጠርና በማጠናከር በገንዘብ ሊደልልና ሊገዛ የሞከረና የከፋፈል ብርሃኑ ነጋ ነው። ከቃሊቲ ተደብቆ ወጥቶ እቤቱ ያድር የነበረው ብርሃኑ ነበር። ከቃሊቲ እስር ቤት ሲወጡ "እንኳን ለዚህ አበቃችሁ" ለማለት እቤቱ የመጡ ሰዎችን መልሶ "ፕራይቬስዬን ነሱኝ" ብሎ በሶስተኛው ቀን አገር ጥሎ ቤተሰቡን ይዞ የኮበለለው ብርሃኑ ነጋ ነው። አሜሪካ ተደብቆ የአፈንጋጩን ቡድን ያጠናከረ እና ሰላሳ ነገር የሚቀባጥረው እርሱ ነው።

የዛሬው ድራማ ደግሞ እነ ብርቱካንን እናንተ "ሰላማዊ ትግል እናካሂዳለን" ብላችሁ በአገር ቤት እኛ ደግሞ በመሳሪያ እንታገላለን ብለን በውጭ ያለውን እንቆጣጠራለን በማለት አሲረውና አስቀድሞ ተመካክረው የተደረገ ነገር ለመሆኑ ማስረጃዎች አሉ። ብርሃኑ ነጋ "ከቅንጅት ተለይተናል" ሲል ብርቱካን ሚዲቅሳ አሜሪካ መምጣቷ ያጋጣሚ ይመስላችኋል? አይደለም። ለተመልካች ሁለት የተለያዩ ድርጅቶች ወይም የትግል መንገዶች የተከተሉ ኃይሎች ይመስላሉ። ወገን አትታለሉ። እነ ብርቱካንና ብርሃኑ ነጋ አንድ ላይ ነው የሚሰሩት። ዋናው ዓላማ የሕዝቡን ስሜት በተለያየ አቅጣጫና መንገድ ይዘው ከትግሉ መንገድ ማዘናጋት፣ እውነተኛውን ትግል ማዳከምና መከፋፈል ነው። ይህንን ለማድረግ ደግሞ በተቀነባበር መንገድ በውጭ መንግሥት አማካኝነትና በወያኔ የረቀቀ መንገድ ተፈቅዶላቸውና አድርጉ ተብለው ነው።

ዞሮ ዞሮ የወያኔን እድሜ ማራዘሚያ፣ ሕዝቡ ተስፋ በእነርሱ ላይ ጥሎ ገንዘቡን፣ ጊዜውንና ጉልበቱን እንዲያውል መጨረሻም ወያኔ ሲያሸንፍ ተስፋ ቆርጦ እንዲገዛ ለማድረግ ነው።

ዛሬ አሜሪካኖች አውቀው ያመጡት ሰው በአገር ቤት ያለው ንግዱ እየተካሄደ ቤት ንብረቱ እያለ ነው ትጥቅ ትግል የሚያካሂደው? ከሰላማዊ ትግል ውጭ አሜሪካ በመሳሪያ የሚታገሉትን ሽብርተኛ ብሎ በሚፈርጅበት ሰዓት ነው ያውም ዲሲ ተቀምጦ ከአስመራ ጦር የሚያንቀሳቅሰው? ጥቂት አስቡና የብርሃኑ ተልዕኮ ምን እንደሆን ትረዱታላችሁ።

ስለሆነም ብርሃኑ ነጋም ሆነ አንጻርጋቸው ጽጌ ማንነታቸውንና ምንነታቸውን አውቆ ማሳፈር እንጂ እንደ እስስት ገላ በሚለዋወጠው ቃላቸው መሸንገልና መታለል አያስፈልግም። ብርሃኑ ነጋ ነው ሰላማዊ ትግልን መምራት ያልቻለ ከአስመራ ጦር አንቀሳቅሶ ወያኔን የሚያሸንፈው? ወይስ እርሱ የፈጠራት ብርቱካን ሚዴቅሳ ነች የኢትዮጵያን ሕዝብ ከወያኔ ነጻ የምታወጣ? የሚያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል ይላሉ አበው። ኢትዮጵያ ያልታደለች አገር ነች። የተማሩ ልጆቿ ሊዋደቁላትና ነጻ ሊያወጧት ሲገባ ሆዳቸው በለጠባቸውና በውጭ ኃይል ተገዝተው አገራቸውን ያጠፋሉ። ወዮላቸው! የሕዝብ ፍርድ አንድ ቀን ይጠብቃቸዋል።

እነ ብርሃኑን ነጋን የማያውቃቸው ካለ እንኳን የቅርቡ ሥራቸው በቂ ነው። እውነተኛ መሪዎች መስለዋችሁ የተታለላችሁ ሁሉ አንዴ ደግማችሁ ታስቡ ዘንድ ጥሪዬን አቀርባለሁ። የተሳሳተ አቋማችሁን አስተካክሉ። በሀሰት ፕሮፓጋንዳቸው መታለል ወንጀል አይደለም ወንጀል የሚሆነው ይህንን እያወቁ መደገፍና መቀጠሉ ነው። ባለፈው ሳምንት ከአሜሪካ ወደ ካናዳ ሄዶ ቀን ስብሰባ ላይ ስለ ሞራል እና ስለ ሌላው የትግል ስልት ሲናገር የነበረው ብርሃኑ ነጋ ለሊት ከሕዝቡ ተደብቆ ናይት ክለብ ሲጨፈር ሰክሮ ሲንገዳገድ የነበረው ሰው "የጦር መሪ ሆኖ" ያዋጋኛል የሚል ካለ ጤነኛ አይመስለኝም።

ስለሆነም መልካቸውን ከሚቀያይሩ የእነ ብርሃኑ ነጋ፣ አንጻርጋቸው ጽጌ፣ ብርቱካንና ግበረ አበሮቿ አታላይ ሥራ ተጠንቀቁ። የሚሰሩት በውጭ ኃይል ታዝው የወያኔን እድሜ ለማራዘም ነውና፡

ሚያዝያ 17 ቀን 2000 ዓ.ም